ይድረስ ለጀርመን ድምፅ ራዲዎ ያማርኛው ክፍል
<u>ቦን/ ጀርመን</u>

ከሁሉ በተቀዳሚ የከበረ ሰላምታችንን በማቅረብ ለጀርመን ድምፅ ራዲዎ ሠራተኞች በመላው እንኳን ለብርሃነ መቀሉ በሰላም በደስታ አደረሳችሁ።
በመቀጠልም ሰኞ መስከረም ፰ ቀን ፪ሺ፲ዓ.ም <<ኢትዮጵያ ፌድድራሊዝምና ግጭት>> በተሰኘ ርዕስ በአቶ ነጋሽ መሐመድ አዘጋጅነት ሁለት ተወያዩዎችን በመጠየቅ የቀረበውን ውይይት፤ ቀጥሎም በመስከረም 14 ቀን ፪ሺ፲ዓ.ም በድጋሜ ሌላ ሦስተኛ ተወያይ አቶ ሙልጌታ አረጋዊ የተባሉትን ጨምሮ የተደረገውን ውይይት አዳምጠን የሚከተለውን ግንዛቤ ጽፈናል።

# ፩ኛ. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ የመንግሥት መዋቅር የለም

የውይይቱ ርዕሰ ጉዳይ "<u>ኢትዮጵያ ፌደራሊዝም እና የጎሣ ግጭት</u>" ከመነሻው ፈጽሞ የተሳሳተ ነው። እርግጥ ነው ከደርግ ውድቀት ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ትግሬ ኢሕአዴግና አጋሮቹ የሽግግር መንግሥት ተብዬው ከተመሠረተበት ማግሥት አንስቶ እሰከ ዛሬ ድረስ በያለበት የጎሣ ማጽዳት፤ የዘር ማጥፋት፤ የጎሣ ግጭቶችና ማፈናቀል ያለማቋረጥ መፈጸማቸውንና በዚሁም በጣም ከፍተኛ የሕይወትና ንብረት መውደሙን በሰፊው ማቅረባችሁ፤ ተወያዩ ዕውቁ የፖለቲካ ተንታኝና ደራሲ አቶ የሱፍ ያሲን የጎሣ ግጭት መንስኤና ያስከተለውን ጥፋት በሰጡት ምላሽና ጥልቅ ግንዛቦት፤ የችግሩን ሥር መሠረት በሐቅ መርምረው መፍትሔውንም በዝርዝር ማቅረባቸው፤ ይልቁንም በሁለተኛው ዙር ላይ ያቀረቡት ተወያይ አቶ ሙሉጌታ አረጋዊ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ከዓለም ውስጥ ልዩ በሆነው <u>የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ፌደራሊዝምና የዘር ፖለቲካ</u> መቼ? እንዴት? በነማንና ስለምን? በማን እንደተፈጠረ ሳይገልጹ በደፈናው ያስከተለውን ጦስ ግን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሰጡት ትንታኔና ገለጻ፤ አመክንዩትና ድምዳሜ ጥሩ ሲሆን፤ ሦስተኛው ተዋዋይ የቀድሞው የኦነግ ዋና መሪና ተዋናይ የነበሩት አቶ ሌንጮ ለረጬት መርዝ ምንም ያለመጸጸታቸው ዛሬም ለአውዳሚው የጎሣ ፌደራሊዝምና የዘር ፖለቲካ ብቸኛ መፍትሔነት ሲያቀነቅኑ መስማት አሳፋሪ ነው። እርሳቸው በተቀዳሚ በኤርትራ ተሰነይ ከተማ ላይ ባረቀቁት የሽግግር መንግሥት "ቻርተር" መሠረት ለኤርትራ ክፍለ ሀገር የመገንጠል ሂደት መመቻቸቱና ቀሪውን የኢትዮጵያ ግዛት በቋንቋና በጎሣ መለያነት እንዲሸነሸን የተዘጋጀው ሰነንድ ተግባራዊ በማድረግ ይታወቃሉ። የሽግግር ወቅቱ ሲያከትምም ሐገ መንግሥት

ተብሎ ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ተሳትፎና ይሁንታ በፀረ ኢትዮጵያ ምዕራባውያን መንግሥታት ትብብርና ድጋፍ በወያኔ ትግሬ አናሳ ጎሣ ቅጥረኛ ቡድን የጠመንዣ ኃይል የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ተጭኖበት ይገኛል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ የመንግሥት መዋቅር የለም። ታዲያ የጀርመን ድምፅ ጋዜጤኛው በአውሮፓ ዕምብርት በተለይም በፌደራላዊ ጀርመን ሪፑብሊክ እየኖረ ጀርመናውያን አንድ ሕዝብ ሆነው እንኳ እንደ ባሕላቸውና ታሪካቸው መሠረት 16 ነፃ ክፌለ ሀገራት ( Die Länder) ናቸው የጀርመንን ፌደራል ሪፑብሊክ ያቆሙት። ጀርመናዊ ዜግነት እንጂ የክፍለ ሀገር ዜግነት እንደ ኢትዮጵያው የጎሣ ፌደራሊዝም ተብዬው የጎሣ ክልል ዜግነት የለም። የዓለም ልዕለ ኃይል አሜሪካም ፌደራላዊ መንግሥት በዘርና በጎሣ መለያነት አልተመሠረተም። በዚያ ያለውም አንድ አሜሪካዊ ዜግነት ነው። የብዙ ነገዶችና ቋንቋዎች አገር ሕንድ ፌደራላዊ የመንግሥት መዋቅር አላት። ሕንድዊ ዜግነት እንጂ የትውልድ ስፍራቸው ያካባቢ መንግሥት ዜግነት የላቸውም። ከሁሉም በለይ በአሜሪካ ይሁን በሕንድ በፌደራላዊው ሕገ መንግሥት አንድም ክፍለ ሀገር የመገንጠል መብት የለውም። በዓለም ላይ አንድ መንግሥት የልዑላዊ ግዛቱን መገንጠል እወቁልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግሥታት አቤቱታ ያቀረበና ወደፊት ለሚበታተኑት በሕግ መንግሥት ደረጃ የደነገገ አገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት። በኢትዮጵያ የወያኔ ትግሬ አናሳ ጎሣ ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ሕገ መንግሥት ሥልጣኑን ለማቆየት አስቦ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሦስት ዕርከኖች ማለትም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መድቦ የመገንጠል መብትን አጽድቋል።

## ፪. የጎሣ ክልል ካርታው ዝግጅት በሰፊው

የኦነግ መሪ የነበሩትና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) መሥራችና መሪ የሆኑት አቶ ሌንጮ ለታ በኢትዮጵያ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተሚያ ከዛሬ 26 ዓመታት ጀምሮ የሰፈነው የባንቱስታን አፓርታይድ <u>የጎሣ ክልል ፌደራሊዝም</u> ተብየው ዋናው መሓንዲስ በመሆን የፈጠሩበትን አካሄድ በውይይቱ ላይ አሳስተው ማቅረባቸው ያስገርማል። ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንደሚባለው የደርግ ወታደራዊ መንግሥት ለ17 ዓመታት በሶሻሊዝም ሽፋን ሕዝብን ሲጨፈጭፍ ቆይቶ፤ ለገንጣይና አስገንጣይ ቅጥረኛ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች እነሻዕቢያ፣ ኦነግ፤ ሕወሓት. ወዘተረፈ ጥርጊያ መንገዱን አዘጋጅቶ በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ወደ ዚምባብዌ እንዲፈረጥጥ በምዕራባውያን በተለይም በአንግሎ-አሜሪካን መንግሥት ባለሥልጣናትና የስለላ ድርጅት የተቀነባበረ ሴራ ተፈጽሟል። በአቶ ኸርማን ኮኸን የተባለ ይሁዲ ፀረ ኢትዮጵያ መሪ ተዋናይነት የኢትዮጵያ ልዑላዊነት፤ ነፃነትና የግዛት አንድነት ለንደን ላይ ተደረገ በተባለው የውሸት ስብሰባ ግባተ መሬት ተከናውኗል።

በአካባቢው አረቦች ርዳታና ትብብር ሲረዱ የነበሩት እነ ሻዕቢያና ወያኔ ሐወሓት እንዲሁም ኦነግ በኤርትራ ተሰነይ ከተማ ተገናኝተው የሽግግር መንግሥት "ቻርተር" አስቀድመው ማጽደቃቸውን አቶ ሌንጮ ለታ ከዚህ ቀደም ለብዙ የመገናኛ ዜና አውታሮች በይፋ ቀርበው እራሳቸው እንዳዘጋጁት አቶ መለሰ ዜናዊና አቶ ኢሳኢያስ አፈወርቂም እንደተስማሙበት ግልጸውልን ከነበረው ጋራ ዛሬ ደግሞ የሚሉት ፈጽሞ ይቃረናል። በአሜሪካን መንግሥትና የስለላ ድርጅት ልዩ ባለሙያዎች በነ ፓውል ሄንዝና ብጤዎቹ አማካሪና ወሳኝነት ኢትዮጵያን ልክ በወራሪው ፋሽስት ሙሶሎኒ ዕቅድ መሠረት በቋንቋ መለያ ለመሸንሸን ከቅጥረኛ አማጺዎች ጋራ ስምምነት የተደረገው ኤርትራ ተሰነይ ከተማ ላይ መሆኑ ሰፊ ማስረጃ አለን። ታዲያ! ስለምን ነው በውይይቱ ላይ <u>አቶ ሌንጮ ለታ የጎሣ ፌደራሊዝም ክልል ለመመሥረት የተጠቀምነው በደርግ ዘመን የተቋቋመውን የብሔረሰብ ኢንስቲትዩት ጥናትን መሠረት በማድረግ ነው</u> እያሉ የተሳሳተ ትርካ የሚያቀርቡት?

አቶ የሱፍ ሐሰን እራሳቸው የብሔረሰብ ኢንስቲትዩት ድርጅት ሠራተኛ ስለነበሩ በርግጥ በድርጅቱ ጥናት መሠረት የባንቱስታን የጎሣ ክልል ያልተመሠረተ መሆኑን ሊያረጋግጡ ይችላሉ።እረ! ለመሆኑ የኦነግ "ኦሮሚያ" ካርታ የተሳለው የደርግ የብሔረሰብ ኢንስቲትዩት ከመቋቋሙ በፊት ኦነግ እንደተመሠረተ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑና በዚህም መሠራት ኦነግ የማይገባውን ሰፊ ግዛት "ኦሮሚያ" ብሎ ከወያኔ ትግሬ ማግኘቱ መሸፈፕ አይቻልም።

ከደርግ ወድቀት መልስ የሰኔው ወር 1983 ዓ.ም ጉባኤ ሲደርግ ከዐማራ ሕዝብ በስተቀር የሌሎች ነሣዎች ታማኝ ተለጣፊዎች ተሰብስበው የሽግግር መንግሥት ተብዬውን ከመሠረቱት ዋና ተዋናይ የአቶ ሌንጮ ለታው ነፃ አውጭ ግንባር ኦነግ እንደነበረ መቼም አይዘነጋም። ከሁሉም በላይ በአቶ ሌንጮ ለታ ዋና ስብሳቢነት የተሰየሙ ኮሚቴ የጎሣ ፌደራሊዝምን ክልል ካርታን እንዴት እንዳተዘጋጀ ሳራ ቫውጋን/ (Sarah Vaughan: Ethnicity and Power in Ethiopia, The niversity of Edinburgh,(2003),PP. 27-39) ያደረገችውን ምርመር እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው።

> <<በቀጠለው ነሐሴ ወር 1983 ዓ.ም የጎሣ ክልል ካርታ አዘጋጅ ኮሜቴ በሽግግር መንግሥቱ ተቋቋመ። አባላቱም አሥር ነበሩ። የተውጣጡትም ከስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲሆን 3 ከኢሕአዴግ፤ 2 ከኦነግ፤ 1 ከጉራጌ፡ 1 ከሃድያ፤ 1 ከሃረሬ፡ 1 ከሱማሌ እና 1 ከአፋር ናቸው። የኦነግ ተወካይ ያማራውን አገር ወሎን አጠቃሎ ለኦሮሚያ ካርታው ለመጨመረ በጠየቀበት ጊዜ የሃድያው ተወካይ በተቃውሞ ተንስቶ ነገሩ እንዲህ ከሆነማ ባሌና አርሲ ታሪካዊ የሐድያ ሲዳማ ምድር በመሆናቸው ወደ ሃድያ መከለል አለባቸው>>

በማለት ስለተቃወመ ብቻ ነው ወሎ ሳይጠቃለል እንደተረፈ የኮሚቴ አባላቱን ጠይቃ ሳራ በሰፊው ዝግባዋለች።

፫ኛ. የጎሣ ክልል፣ የጎሣ ማጽዳትና የዘር ማጥፋት

የጎሣ ማጽዳትና የዘር ፍጅት የተጀመረው ከሰኔው ወር 1983 ዓ.ም ጉባኤ አምስት ቀናት በኋላ በድሬ ደዋ ከተማ በተነሳ የጎሣ ግጭት 35 ዐማራዎች ተገድለዋል። ቀጥሎም በሐረርጌ ጋራ ሙለታ አውራጃ ከ96 በላይ ዐማሮች ቤት ንብረታቸው ተቃጥሏል፤ ተዘርፈዋል፣ ሴት፣ ሕፃናት፤ አዛውንት በአረመኔ ሁኔታ ተገድለዋል። በወበራ፣ በሐብሮ በጨርጨር ወዘተረፈ አውራጃዎች ዐማሮችና ክርስቲያኖች ተጨፍጭፈዋል። በተለይም በበደኖ ከተማ የተፈጸመው እጅግ አረመኔ ድርጊት ፈጽሞ አይዘነጋም። በአሩሲ አርባጉጉ አውራጃ፣ በባሌ፣ በደቡብ ሸዋ ቀጥሎም በወለጋ፣ በከፋ፣ በማጂ ወዘተረፈ የብዙ ሚሊዎን ያማራ ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ወድሟል። ለዚሁ ሁሉ ጥፋትና ወንጀል ዋና ተጠያቂዎቹ ወያኔ ትግሬ፣ ኦነግ እና ኦሕዴድ ናቸው። አቶ ሌንጮ ለታ የሽግግር መንግሥት ተብዬው አካል በመሆን በዐማራ ሕዝብ ላይ ለፈጸሙት የጎሣ ማጽዳትና የዘር ፍጅት ተጠያቂ ናቸው። የወያኔ ትግሬ ዐማርኛ ተናጋሪው ጉጀሌ ቡድን ኢሕዴን ተብዬው ቀንደኛ መሪ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበረውና ኋላ ግን የስኳር ሌባ ሆኖ ዘብጥያ የወረደው ታምራት ላይኔ የተባለው ፀረ ዐማራ በሐረርና በጅጅጋ ከተማ እንዲሁም በአዋሳ ለተሰበሰበው ሕዝብ ፀረ ዐማራ ቅስቀሳ በማድረግ፤ በዐማራ ተወላጅ "ነፍጠኞች፤ ትምክህተኞች፤ በዝባዦችና ቅኝገዥዎች" ላይ ነፃ እርምጃ እንዲወስዱ ሰፊ ቅስቀሳ አድርጓል። ሌላው ቅጥረኛ የኦሮሞ ክልል ፕሬዘደንት ተብየው የወያኔ ትግሬ ተላላኪ ውሻ አሊ ሐሰን "ዐማራን ከምደረ ገጽ ለማጥፋት ወቅቱ አሁን ነው" እያለ ሲንደክደክ የነበረው ዛሬ በስደት ባሜሪካ ቢገኝም ከፍርድ ከቶ በጭራሽ አያመልጥም።

## ፬ኛ የብሔሮች የረስን በራስ ማስተዳደር መብት እስክ መገንጠል

ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ እንመለስ የጎሣ ፌደራሊዝም ክልል ተብዬውና የብሔሮች የራስን በራስ መወሰን መብት እስከ መገንጠል መብት የሚለውን የአውሮፓ ኮሚኒስታዊ መርህ ተከትሎ የኢትዮጵያን ብቸኛ ጥንታዊ አገርና መንግሥት አሶግዶ በባንቱስታን አፓርታይድ የዘር ፖለቲካ ሐዝቡን በቋንቋና በዘር መለያ ልክ እንደ ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን አለያይቶ ለመግዛት ታስቦ ነው እንጂ በኢትዮጵያ ምድር ለሚኖሩ ልዩ ልዩ ነገዶችና ማኅበረሰቦች እኩልነት፣ በደሞክራሲያዊ ነፃ ምርጭያ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትና ነፃነት፤ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ልማት በተጨባጭ ለማረጋገጥ ሳይሆን በከፋፍለህ ግዛ የእጅ አዙር ቅኝተገዥነትን፣ እስትራቴጂዊ ቁልፍ ስፍራ በሆነው የሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ አካባቢ የአባይ ሸለቆና ዋና የንግድ

መስመር የቀይ ባሕር ሕንድ ውቅያኖስን ለመቆጣጠር በሰፊው የታቀደ ሴራ ነው። በመሆኑም ነው የኢትዮጵያ የሩቅና የቅርብ ታሪካዊ ጠላቶች ለረጅም ዘመናት በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በጦር ኃይል ወረራ ያደረጉት። ይልቁንም ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር በአጤ ምኒሊክ መሪነት ተባብረው በአድዋ ላይ ድል ከተቀዳጁ ወዲህ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ስልትና ዘዴ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ታቅዶ በትውልድ ኢትዮጵያዊ በሆኑት ቅጥረኛ ባንዶች ተግባራዊ የሚሆንበትን ያጭርና የረጅም ዘመን ዕቅድ አዘጋጅተዋል።

በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዋዜማ በ1927 ዓ.ም የአውስትሪያው (ነምሳ) ተወላጅ ናዚ ባሮን ፍራየኸር ፕሮቻዝካ የተሰኘው የነጭ ዘር የበላይነት አቀንቃኝ በአዲስ አበባ ቆይቶ ሲመለስ በጻፈው ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ጥቁር መጽሐፉ <u>አበሻ፣ ጥቁ ር አደጋ</u> (Abyssinien: Die Schwaarze Gefahr,, Saturnverlag / Wien, 1935 ) በገጽ 11 ላይ አፍሪቃ ያስፈራራል! በሚለው ምዕራፍ፤

> <<በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ነገዶችና ሕዝቦች በአናሳው አበሻ በኃይል ተይዘው ይኖራሉ። ከአበሻው ጋራ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በባሕል ልዩ የሆኑት <u>የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ቢሰጣቸው</u> ኖሮ ያበሻን በግዳጅ መግዛት ባሶገዱት ነበር። ይሁንና ከአውሮፓውያን የባሕልና ቅኝ ተገዥነት ከሚያመጣው ልማትና እድገት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በኃይል ተገደዋል።>>

በማለት የኢትዮጵያ ነገዶች ሁሉ እንደሌሎች አፍሪቃውያን ቅኝተገዥ ባለመሆናቸውና ለነጭ የማያደገድጉ መሆናቸው ቀንድ ያስበቀለው በጣም ወራዳ ናዚ የነበረው የጻፈውን የጥላቻ ሐተታ ይገነዘቧል። በተለይም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ፀረ ነጭ፣ በአፍሪቃ ፀረ ቅኝገዥዎች አቋም መያዝ ጀምሯል። ወጣት ኢትዮጵያውያን በጣም አደገኛ የኢትዮጵያዊነት ስሜት አራማጆች ናቸው። ከአፍሪቃ አልፎ ከጃፓን ጋራ ግንኙነት በመፍጠር ፀረ ነጭ ዘር እንቅስቃሴና ትብብር ያደርጋል፤ ይመራል፤ ወዘተረፈ እያለ የፀረ ኢትዮጵያዊነት እንቅስቃሴ በጣም ሰፊ ፕሮፓጋዳ ነዝቷል። ኢትዮጵያን በወታደራዊ ዘመቻ እንዴት ወሮ መያዝ እንደሚቻልም ሰፊ ትንተና ለፋሽስት ጣሊያን ወራሪዎች አቅርቧል። በደር አገርና በጠረፍ ያሉትን የጎሣ አባቆሮችና ባላባቶች ለአውሮፓውያን ቅኝገዥዎች ታማኝ አገልጋይ በማድረግ ብቻ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ማድረግ እንደሚቻል በአጽንኦት አሳስቦ ነበር።

ስለዚህም ነው ፋሽስት ጣሊያን ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ስልት በመከተል ከሰሜንና ከደቡብ ምሥራቅ በኩል በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም ወረረች። የሐማሴንና የሱማሌ አስካሬዎችን በብዛት መልምላ አሰልፋዋለች። ነገር ነጻነት ወዳዱ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባርጌ መሰሪያው ከጠላቶች ፋሽስት ጣሊያኖችና አስካሪ ባንዳዎች ጋራ ተጋጥሞ ለሃገሩ ተሰውቷል። ቡከን ሰላቶ ጣሊያን በምደር ጦር ውጊያ ግንባር ደባቅ ሲመታ በኬሚካል መርዝ በአየር እየረጨና በዘመናዊ የጦር መሠሪያና ትጥቁ

ብዛት እንዲሁም በከሃዲዎቹ የራያና የትግሬ ባንዶዎች ከፍተኛ ርዳታ ትብብር የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞችን ብቻ ለአምስት ዓመታት ይዞ ቆይቷል። በአንጻሩም አርበኞች በመላው አገር የጎበዝ አለቃቸውን መርጠው ሰላቶንና ባንዳን መውጭያ መግቢያ አስጥተው ነፃነታቸውን አስከብረው ፋሽሽት ጣሊያንን ድባቅ መተውታል። በድላችን ዋዜማ እንግሊዞች ልንረዳችሁ መጣን ብለው ጣሊያን ያስገባውን፣ የተከለውን ሃብት ንብረት ዘርፈው ወስደዋል። ከዚህ ሌላ ስምምነታቸውን አፍርሰው በኢትዮጵያ ቅኝገዥ ሞግዚት ለመሆን ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። በሰሜን ኢትዮጵያ ትግሬና ኤርትራን አንድ አድርገው (የትግራይ-ትግርኝ)፣ በደቡብ ምሥራቅ ደግሞ የኡጋዴን አውራጃን ከኢትዮጵያ ገንጥለው በመውሰድ የታላቋ ሰማሌ በእንግሊዝ ሞግዚትነት ሥር የአፍሪቃ ቀንድን ለመቆጣጠር ተመኝታ ስትኳትን የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ባደረሰባት ከፍተኛ ኪሣራ ከብዙው የዓለም ክፍል ቅኝገዥነቷ ተንኮታኩታ ወደቀች። በአሜሪካን ልዕለ ኃያል ጥላ ሥር ተጠለለች።

ያጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከአሜሪካ መንግሥት ጋራ በመወዳጀት ከዜሮ ተንስተው የኢትዮጵያን መንግሥት በሁሉም ረገድ ታላቅ ርምጃ ማድረጋቸው አሌ አይባልም። ነገር ግን ያጤ ኃይለሥላሴ መንግሥት በከፍተኛ ጥረት ያስተማሩት ትውልድ በውጭ ባሕልና እምነት የተበከለ ነበር። በተለይ በ1960ዎቹ ዓመታት የተከሰተው የተማሪዎች እንቅስቅሴና የፈጠረው የብሔረሰብ የራስን በራስ መወሰን እስከመገንጠል መብት ዓላማውና ግቡ ያጤ መንግሥት በከፍተኛ ፖለቲካዊ ትግልና በኤርትራውያን ተወላጆች ትብብር ኤርትራ ተመልሳ የመዋሃዷን ሂደት ለማስገንጠል በአካባቢው አረቦችና አገር በቀል ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች የተቀነባበረ ሴራ ዋና አራጋቢ እንደነበርና ኢትዮጵያ አሁን ለምትገኝበት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ተጠያቂ መሆኑን አወያዩ ጋዜጠኛ "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከ1960ዎቹ ጀምሮ የታገሉለት፤ የሞቱለት፣ የታሰሩለት የብሔር ብሔርሰቦች ጥያቄ መልስ አግኝቶ ነበር" በማለት የተረከው የዚያ ቅጥረኛና ደንባራ ትውልድ አድናቂና ደጋፊ መሆኑ በግልጽ ታይቷል። ጥቂት ተማሪዎች በአስመሳይ ማርክሳዊ ሌኒናዊነት መርህንና የቬትናም ብሔረተኛ መሪ ሆችሚን "መሬት ላራሹ" መፈክርን በማስተጋባት ሲያደርጉት የነበረው እንቅስቃሴ ዋና ዓላማውና ግቡ ያጤውን መንግሥት የአስተዳርና የፍትሕ ጉድለት ለማቃናት ሳይሆን በሥር ነቀል ለውጥ ሽፋን ሥልጣን ባቋራጭ ለመያዝ እንዲሁም ዐማራውን ሕዝብ ለይተው ክርስቱና የግል ሃብት ይዞታው ለመንቀል የተመረጠ ስልት ነበር።

የተማሪ እንቅስቃሴ ተብየው በአገር ቤትና በውጭ የነበረው ተጠልፎ በሁለት የጎቡዕ ኮሚኒስት ፓርቲዎች (መኢሶንና ኢሕአፓ) ቁጥጥር ሥር ሆኖ እያለ ነው የየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ሕዝባዊ አመጽ የተቀሰቀሰው። በተከሰተው አመጽ ምክንያት ወታደራዊው የጦር ኃይል ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ኢትዮጵያ ወዲያው ትበታተን ነበር።

ወታደራዊ ደርግ ቀስ በቀስ ተጉዞ ሥልጣንን በመስከረም ወር 1967ዓ.ም ሲይዝ ያጤው መንግሥትም አከትሟል። ደርግ ተመሥሮቶ የአገሪቱን ዳር ድንበር ለመጠበቅ በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ሆኖም ግን የፖለቲካ ፍርጎው ባዶ

ስለነበር ይህኑ ለመሙላት የፈለጉት ወገኖች አስቀድመው በውጭ አገር በኅቡዕ ከተማሪው እንቅስቃሴ ወጥተው የተደራጁት ሁለቱ የኮሚኒስት ፓርቲዎች (መኢሶንና ኢሕአፓ) በፍጥነት ገስግሰው አዲስ አበባ በመግባት በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም የጦር ኃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ ያወጣውን ባለአሥር ነጥብ አቋም አስለውጠው ደርግን ከጥልቅ ፖለቲካ አዘቅት ውስጥ ከተውታል። ሁለቱ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ሥልጣን ለብቻቸው ለመያዝ ግብግብ ጀመሩ። በመካከላቸው የነበረው ከፍተኛ ሹኩቻና ንትርክ ወደ ጦርነት ተቀይሮ በቀይና በነጭ ሽብር በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ምሁራን፤ ተማሪዎች፤ ሠራተኞች በከንቱ ደማቸው ፈሰሶ ቀርቷል። መኢሶን የነበረው አቅም መጠናኛ በመሆኑ ምክንያት ከደርጉ ጋራ ወግኖ ነበር። ኢሕአፓ ግን ተማሪውንና አስተማሪውን መሠረት በማድረግ ሥልጣንን ከደርግ ለመውሰድ የትግል ስልቱ የከተማ ፋኖ ጦርነትን በደርግና መኢሶን አባላት ላይ መክፈት ነበር።

የተማሪው እንቅስቃሴ ፋሽስቶችና ናዚዎች ፀረ ጥቁር፤ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች እነ ፍራየኽር ፕሮቻዝካ ያቀነነቀኑትን የጎሣና የዘር ፖለቲካን በስታሊናዊው መፈክር፣ የብሔርሰብ የራስን ዕደል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል መብት መጠቅለያ ጨንበል ሸፋፍነው ኢትይጵያ የሚባል አገር (ብሔር ) የለም፤ ባሕል፣ ታሪክ፤ ማኅበረሰብ የለም። ኢትዮጵያዊነት ያማሮች የፈጠራ ወሬ ነው። ያለው የኦሮሞ ብሔር፣ የሱማሌ ብሔር፣ የትግሬ ብሔር፣ የጉራጌ ብሔር ወዘተረፈ ነው። ኢትዮጵያዊ ለመሆን ሸማ መልበስ፡ እንጀራ መብላት፤ ያማርኛ መዚቃ መጭያዎትና የእርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት አማኝ መሆንና ዐማርኛ ቋንቋ መናገር ካልቻልክ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ትብሎ ፀረ ዐማራ ቅስቀሳ ተነዛ። በሩሲያ እነ ሌኒንና እስታሊን የሩሲያን ሕዝብ ለይተው ጨቋኝ ብሔር እንዳሉት በኢትዮጵያ ደግሞ አስመሳይ በቀቀኖች በወሬ በሰሙት ኩረጃ ዐማራውን ሕዝብ ለይተው ጨቋኝ ብሔር፤ ትምክተኛ፤ ፊውዳል፤ አድሃሪ ብለው ፈረጁት። ሌሎች ጎሣዎች ደግሞ ጭቁን ብሔር ተባሉ።

በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በአፍሪቃ አህጉር በመላው ቅጥረኛ የነፃ አውጭ ግንባር ተብዬዎች እንደ ሕወሓት፤ ሻዕቢያ፣ ኦነግ፣ ዩኒታ ወዘተረፈ. የመሳሰሉት የምዕራባውያኑ በተለይም የአንግሎ አሜሪካን ስለላ ድርጅቶች ተቀጣሪነታቸውን እንደ ማዕከላዊ አሜሪካ ኒካራጉዋ ኮንትራዎች መሆናቸውን ለምሳሌ ሕወሓት በአልባኒያ ሶሻሊዝም፤ በማርክስ ሌኒናዊ ጨንበል ጀቡኖ ነው ከለንደን ከተማ ዋና ቢሮአቸው ፀረ ሶቪየት ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ሲነዙ የነበረው። ፕሬዘዳንት ሮናልድ ሬገን ፀረ ኮሚኒስት ድርጅቶችን ከመላው ዓለም በሰብሰበበት ወቅት፣ ሕወሃት ከነኮንትራዎች፣ ከአንጎላ ዩኒታ፣ ከሞዛምቢክ ወዘተረፈ የተጠሩት ተገኝተዋል። የሮናልድ ሬገና የወይዘሮ ታቸር እንግሊዝ መንግሥት በዘመነ ደርግ ከፍተኛ ርሃብ ሲከሰት የምግብ ርዳታ በመከልከል እንደ አጤው መንግሥት በወሎና ትግሬ ርሃብ ምክንያት የደርግ ኮሚኒስት መንግሥትም ይወድቃል ብለው ሲጠባበቁ ጋዜጠኞች ኮረምና ትግሬ ሄደው ያነሱትን ያላም ሕዝብ አይቶ ስላወገዛቸው ነው ርዳታ መላክ የጀመሩት። የስለላ የጦር አውሮፕላኖች ምግብ ጭነው ወደ አዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ የበረሩትና ከሰማይ ላይ ምግብ እንጥላለን ብለው መረጃ እየሰበሰቡ ለአማጽያን ተብዬ ቅጥረኞቻቸው ወታደራዊ መረጃ ያቀረቡት።

---


እነ ገለበው ሰንገጎ   መክብብ በየነ   አስካለ ገበየሁ   ደስታ በላይ
የውብዳር ዘለቀ   ደርቤ በዳሳ   ገሞራው ማንያዘዋል

tomy. gemora16@gmail.com